NAFYAD SCHOOL

2 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 CIVIC 2

መመሪያ አንድ፡- ከተሰጡት አራት አማራጮች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁር/ሪ

1. ዴሞክራሲን በተመለከተ ትክክል የሆነው ሃሳብ የትኛው ነው?
   A. በህዝብ ፍላጎት እና ምርጫ ላይ የተመሰረተ አስተዳደር ነው።
   B. የስልጣን ምንጭና ባለቤት መንግስት የሆነበት ሥርኣት ነው።
   C. የመንግስት ሥርኣት ሲሆን የሚያገለግለውም የመንግስትን ባለስልጣናት ነው።
   D. የሚጠቅመው በጣም ለተማሩና ለሰለጠኑ ህዝቦች ብቻ ነው።
2. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 35 ላይ የተደነገገው የሴቶች የልዩ ድጋፍ መብት አላማ የሆነው የትኛው ነው?
   A. የሴቶችን የበላይነት ለማረጋገጥ
   B. የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳነስ
   C. በሴቶች ላይ ሲፈፀም የነበረውን አድሎኦ በማስወገድ የዶታ እኩልነትን መረጋገጥ
   D. የወንዶችን የበላይነት ለማረጋገጥ
3. ከሚከተሉት መካከል የስልጣን ገደብ ባለመኖሩ ምክንያት ሊከሰት የሚችለው ችግር የቱ ነው?
   A. ግልፅነትና ተጠያቂነት አይኖርም
   B. ህግና ደንብ ተገቢ በሆነ መልኩ ስራ ላይ ይውላል
   C. ተበዳዮች ቅሬታቸውን እንዲያቀርቡ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።
   D. መልሱ አልተሰጠም
4. የአንድ ዜጋ ዴሞክራሲያዊ መብት ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?
   A. ያለምርጫ ስልጣል መያዝ
   B. ሃሳብን በነፃነት መግለፅ
   C. ሀይልን መጠቀም
   D. የሌሎችን መብት መጣስ
5. የሲቪክ ማህበራት የሚመሰረቱበት አላማ ምንድ ነው?
   A. ለትርፍ
   B. ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት
   C. የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ
   D. ሀይማኖታዊ ትምህርትን ለማስፋፋት

6. የአመለካከት ድህነት ማለት

   A. ራስን መውደድ ማለት ነው

   B. ለጋራ ጥቅም ማሰብ መተው ነው

   C. ኃ ላቀር ልምዶችን ማዳበር ማለት ነው።

   D. ሁሉም መልስ ናቸው

7. ከሚከተሉት ውስት የአይነት ቁጠባ ያልሆነው የቱ ነው?

   A. ቤት B. መኪና C. እውቀት D. መልሱ አልተሰጠም

8. በውይይት ወቅት አንድ ሰው ማድረግ የሌለበት የቱን ነው?

   A. የውይይቱን ርዕስ ጉዳ ቀድሞ ማወቅ

   B. የራስን ሃሳብ ሌሎች እንዲቀበሉ ጫና ማድረግ

   C. ውይይትን በጥሞና እና በሰላም ማከናወን

   D. መቻቻልና መተጋገዝ

9. የኤ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርህ ያልሆነው የቱ ነው?

   A. የህገመንግስቱ የበላይነት

   B. የባለስልጣናት ሉዓላዊነት

   C. የመንግስት አሰራርና ተጠያቂነት

   D. የመንግስትና የሃይማኖት መለያየት

10. የእኩልነት መብቶች አለመከበር የሚያስከትለው ችግር

   A. የእርስ በእርስ ግጭትና አለመግባባት

   B. ድህነትና ኃላቀርነት

   C. የህጎች ጥሰትና አድሎአዊነት

   D. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

11. ከሚከተሉት ውስጥ ኃላፊነትን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   A. ኃላፊነትን መወጣት ከራስ ይጀምራል

   B. ኃላፊነትን የሚወጡት የመንግስት ባለስልጣናት ብቻ ናቸው

   C. በቤተሰብ ውስጥ ኃላፊነትን መወጣት አያስፈልግም

   D. ኃላፊነትን መውሰድ ማለት ኃላፊነትን መወጣት ነው።

12. የኢ.ፊ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት የልማትና የኢኮኖሚ አላማ ያልሆነው የቱ ነው?

A. ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ

B. በከፍተኛ ደረጃ ህዝቡን የልማት ተጠቃሚ ማድረግ

C. ሀገርን ከልመናና ከጥገኝነት ለማላቀቅ የውጭ ግንኙነትን ማቋረጥ

D. ነፃ የገበያ እና የኢኮኖሚ ስርዓትን መዘርጋት

13. ከሚከተሉት ጠንካራ የስራ ባህልን በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ስራን አለመናቅ B. የጊዜ አጠቃቀምን አለማወቅ C. በእቅድ መመራ

14. ፍትሐዊነት ማለት

A. ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ነው B. በጉቦ መስራት ነው

C. ለእውነት አለመቆም ነው D. አድሎአዊ አሰራርን ማስፈን ነው

15. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የዜጎችን የሀገር ፍቅር ስሜት አይገልፅም

A. ትምክተኝነት B. ጠባብነት C. አሸባሪነት D. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

16.በዴሞክራሲያዊ ሥርኣት የመንግስት ስልጣን በሶስት አካላት እንዲከፋፈል የተደረገው ለምንድነው?

A. የኃላፊነትና የተጠያቂነትን አሰራር ለማጎልበት

B. ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመፍጠር

C. ለመንግስት ስልጣን ለመጨመር

D. የአንድን ፓርቲ የበላይነት ለማጉላት

17. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በህዝብ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የሚፀድቀው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ነው ?

A. በ 48 ሰዓት ወይም በ 15 ቀናት B. በ 24 ሰኣት ወይም በ 5 ቀናት

C. በ 24 ሰዓት ወይም በ 1 ወር D. ማቅረብ አያስፈልግም

18. ከሚከተሉት ውስጥ ብክነትን የሚያስከትለው የትኛው ነው?

A. በእቅድ መመራት B. ያለአግባብ የሆነ ግብጣን መተው C. ደባል ሱስ D. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

19. እውቀት አገልግሎት ላይ የሚውልበት መንገድ የሆነው የቱ ነው ?

A. ለፈጠራ B. ለምርምር C. ራስን ለማሻሻል D. ሁሉም መልስ ናቸው

20. በፌደራል ደረጃ ህግ አውጪ አካል፣

A. የፌዴሬሽን ምክር ቤት B. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት C. የሚኒስቴሮች ምክር ቤት D. ጠቅላይ ፍርድ ቤት

21. የሃይማኖት እኩልነት አለመከበር የሚያስከትለው ችግር

A. ግጭትና አለመግባባትን ያስከትላል B. በሰላም በፍቅር አብሮ ለመኖር

C. የመቻቻል ባህልን ለማዳበር D. አድልኦና ተፅእኖ እንዳይኖር ለማድረግ

22. ለህግና ለህገመንግስት መገዛት የሚለው ሃሳብ ከሚከተሉት ፅንሰ ሃሳቦች በቀጥታ ከየትኛው ጋር ይገኛል?

A. ግልፅነት B. የህግ የበላይነት C. ትምክተኝነት D.ፍትሐዊነት

23. ከሚከተሉት የዜጎች ባህሪያት ውስጥ ላንቁቃ ህዝባዊ ተሳትፎ የጎላ አስተዋፅኦ የሌለው የቱ ነው?

A. ተነሳሽነት B. ፍቃደኝነት C. ግለኝነት D. ተግባራዊነት

24. እ.ኤ.አ ከ 1991 ጀምሮ በኢትዮጵያ ያለው የመንግስት አደረጃጀት ------ ነው።

A. ፌዴራላዊ B. አሃዳዊ C. ኮንፌዴራላዊ D. አንባገነናዊ

25. ድህነትና ኃላቀርነትን ለማጥፋት ሀገራችን እየተከተለች ያለችው የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ የቱ ነው?

A. ግብርና መሪ የልማት ፖሊሲ B. ስራ አጥላትን ማጥፋት

C. አግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መሰጋገር D. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

26. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከአንድ ተማሪ የሚጠበቅ ኃላፊነት አይደለም

A. የተሰጠውን የቤትና የክፍል ስራዎች በአግባቡ መስራት

B. የትምህርት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

C. ትምህርት ቤቱን ማስተዳደር

D. በትምህርት ቤቱ ህግና ደንብ መመራት

27. ከሚከተሉት ውስጥ የሙያ ችሎታን ለማሳደግ አስፈላጊ ያልሆነው የቱ ነው ?

A. የተለያዩ ስልጠናዎችን አለመውሰድ B. የትምህርት ደረጃን ማሻሻል

C. ከሰፎች ልምደም መቅሰም D. የማንበብ ልምድን ማዳበር

28. በአውሮፕላውያን ቀኝ አገዛዝ በፊት በአፍሪካ ውስጥ በአብዛኛው ይታይ የነበረው መስተዳድር የቱ ነበር?

A. ባህላዊ መስተዳደር B. ቅኝ ግዛታዊ C. ዴሞክራሲያዊ D. ዘውዳዊ

29. በልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የህብረተሰቡ ተሳትፎ መታየት የሌለበት በየትኛው ደረጃ ነው ?

A. እቅድ በማውጣት B. እቅድ በማስፈፀም C. እቅድ በመገምገም D. በእቅዱ አለመመራት

30. የአንድ ሀገር የውጭ ግንኙት ፖሊሲ መሰረት የሚያደርገው ምንን ነው ?

A. ታሪካዊ ግንኙነትን B. የመንግስት ፍላጎትን C. የሀገር ጥቅምና ሉዓላዊነትን D. ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥን

31. የእኩልነት መብቶችን በተመለከተ የተሳሳተ ሃሳብ የያዘው የቱ ነው?

A. የአካል ጉዳተኞችን መብት ማክበርና ማስከበር የመንግስት ኃላፊነት ብቻ ነው።

B. የእኩልነት መብቶች አለመከበር በዜጎች መካከል የበላይነትና የበታችነት ስሜት እንዲኖር ያደርጋል

C. የሴቶችን መብት ማስከበር የሕብረተሰቡን መብት ማስከበር ማለት ነው

D. እኩልነት ባልሰፈነበት ሀገር ውስጥ ሰላምና ልማት አይኖርም

32. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት ማንኛውም የክልል ህገ መንግስትም ሆነ ሌሎች ህጎች የፌዴራሉን ህገ መንግስት በሚቃረን መልኩ የሚደነገጉ ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።ይህ ድንጋጌ በየትኛው አንቀፅ ላይ ይገኛል?

A. አንቀፅ 8 B. አንቀፅ 39 C. አንቀፅ 9 D. አንቀፅ 98

33. ከሚከተሉት ውስጥ ዘመናዊ የቁጠባ ስልት የሆነው የቱ ነው?

A. እቁብ B. ባንክ C. እድር D. ማህበር

34. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት ስንት ምዕራፎችና አንቀፆች አሉት?

A. 11 ምዕራፎችና 106 አንቀፆች B. 11 ምዕራፎችና 105 አንቀፆች

C. 101 ምዕራፎችና 61 አንቀፆች D. 13 ምዕራፎችና 106 አንቀፆች

35. ራስን መቻል በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ?

A. መሰረታዊ ፍላጎትን ማሟላት B. ከጥገኝነት መላቀቅ C. ሳይሰሩ መብላት D. በራስ መተማመን

36. በኦሮሚያ ክልል የማይገኘው ታሪካዊ ቅርስ የቱ ነው?

A. የአባ ጅፋር ቤተ መንግስት B. የፋሲል ቤተ መንግስት

C. የኩምሳ ሞሮዳ ቤተ መንግስት D. የሼክ ሁሴን መስጊድ

37. የፍርድ ቤቶች ነፃነት ማለት

A. የህግ ባለሞያዎች ከህግ በላይ መሆን B. የፍርድ ቤቶች ስልጣን ገደብ የሌለው መሆን

C. ፍርድ ቤቶች ዳኞች በህግ ብቻ የሚመሩ መሆናቸው D. የፍርድ ቤት ዳኞች ከህግ በላይ መሆን

38. የአንድ ሉዓላዊት ሀገር መገለጫ የሆነው የቱ ነው ?

A. መዝሙር B. ሰንደቅ አላማ C. ባህል D. ሐውልት

39. ባህላዊ የፍትህ ስርዓት የሆነው የቱ ነው?

A. የሀገር ሽማግሌዎች B. ፖሊስ C. ፍርድ ቤት D. አቃቢ ህግ

40. ራስን ለመቻልና በራስ ለመተማመን ምን ያስፈልጋል?

A. የራስን እውቀትና ችሎታ ለይቶ ማወቅ B. ራስን መሆን C. በአቋም መፅናት D. ሁሉም መልስ ናቸው

41. ከሚከተሉት መካከል የተሸለ የእውቀት ምንጭ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው ?

A. ቴሌቪዥን B. ቃላዊ መረጃ C. ትምህርት ቤት D. የስብሰባ ላይ ውይይት

42. የክልል መንግስታት ስልጣንና ተግባር ያልሆነው የቱ ነው?

A. የሀገሪቱን ህገ መንግስት ማክበር B. ክልላዊ መስተዳድርን ማፋቀር

C. የክልል መከላከያ ስራዊትን ማደራጀት D. ራስን በራስ ማስተዳደር

43. ከሚከተሉት እንደ ዜጋ ከሰዎች የሚጠበቅ መልካም ስነ-ምግባር ያልሆነው የቱ ነው ?

A. የሰዎችን መብት ማክበርና ማስከበር B. መብትን በጉልበትና በኃይል ማስከበር

C. የመቻቻል መርህን መከተል D. ሀቀኝነት

44. አንድ ሰው ራሱን በብቃት ለመምራት የማያስችለው መርህ የቱ ነው ?

A. አላማ ፍላጎት መኖር B. ራዕይ መኖር C. ፅናት D. ቸልተኝነት

45. ሙስናን ለመከላከል አስተዋፅኦ ማድረግ የማይችለው አካል የቱ ነው ?

A. የፍትህ ተቋማት B. ህዝብ C. መንግስት D. መልሱ አልተሰጠም

46. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር መሰረት በክልል መንግስታት ደረጃ ህግ የማስፈፀም ስልጣንና ኃላፊነት

የማን ነው?

A. የክልል ምክር ቤት B. የክልሉ መስተዳደር

C. የክልል ፍርድ ቤቶች D. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን

47. ከሚከተሉት የአቃቢ ህግ ተግባር ያልሆነው የቱ ነው?

A. ህግ ሲጣስ የተጣሰውን ህግ ያስከብራል

B. ወንጀለኛን ተከታትሎ በቁጥጥር ስር ያውላል

C. የፖሊስ ምርመራን መሰረት አድርጎ ክስ ይመሰረታል

D. በተከሳሾች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ይከታተላል

48. ኃላቀር አስተሳሰቦች ሊቀየሩ የሚችሉት መቼ ነው?

A. ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲስፋፋ B. ለቃል መረጃ የበለጠ ትኩረት ሲሰጥ

C. ባህላዊ ትምህርት ሲስፋፋ D. መልሱ አልተሰጠም

49. የመንግስት የስልጣን አካል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ህግ አውጪ B. ህግ አስፈፃሚ

C. ህግ ተርጓሚ D. መልሱ አልተሰጠም

50. ከሚከተሉት ግብር ያልተጣለበት ገቢ የቱ ነው?

A. ከንግድ ስራየሚገኝ ገቢ B. ከወለድ የሚገኝ ገቢ

C. ከአክሲፎን ድርሻ የሚገኝ ገቢ D. ከጡረታ ጥቅም የሚገኝ ገቢ

51. በህይወት የመኖር መብት፡-

A. የግለሰብ ሰብዓዊ መብት ነው B. የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብት ነው

C. የቡድን ሰብዓዊ መብት ነው D. የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብት ነው

52. ተጠሪነቱ ለፌደራል መንግስት የሆነው ከተማ የቱ ነው?

A. አዳማ B. ፊንፊኔ C. ጅማ D. ባህርዳር

53. በአንድ ሀገር ዜጎች መካከል የሚካሄድ ጦርነት ምን በመባል ይጠራል?

A. የእርስ በርስ ጦርነት B. የቡድን ጦርነት C. የውጭ ወረራ D. የባለስልጣናት ሽኩቻ

54. መልካም አስተዳደር ተጓድሏል ሊያሰኙ ከሚችሉት መካከል አንዱ

A. የአድሎአዊ አሰራር B. የሙስና መንሰራፋት C. የባለጉዳዮች መጉላላት D. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

55. የዶታ እኩልነትን በተመለከተ ስህተት የሆነው የቱ ነው?

A. ሴቶች ከወንዶች እኩል የራሳቸውን አመለካከት ማራመድ መብት አላቸው

B. የሴቶች የመምረጥ መብት እንጂ የመመረጥ መብት የላቸውም

C. በትዳርና በንብረት ጉዳይ ሴቶች ከወንዶች እኩል የመወሰን መብት አላቸው።

D. መልሱ አልተሰጠም

56. የቀጥተኛ ዴሞክራሲ ተሳትፎን የማያሳየው የቱ ነው ?

A. በአካባቢ ልማት መሳተፍ B. ረፈንደም C. በፓርላማ ውስጥ መሳተፍ D. ጓደኛ መምረጥ

57. የሲቪክ ማህበራትን አስመልክቶ የትኛው ትክክል ነው?

A. በሀገሪቱ ህግ የመተዳደር ግዴጅ የለባቸውም

B. በህጉ መሰረት መመዝገብ እና ፈቃድ ማግኘት አለባቸው

C. ከልማት ጎን ለጎን የፖለቲካ እንቅስቃሴ እና እምነት ያካሂዳሉ

D. መልሱ አልተሰጠም

58. የፌደራልን የክልል መንግስታት አላማን ግንኙነት በመጀመሪያ ደረጃ የተመሰረተው በምን ላይ ነው?

A. የውጭ ጉዳዮች ላይ በማትኮር B. የሀገሪቱን ህገ መንግስት በማክበር

C. በጎረቤት ሀገሮች ጣልቃ በመግባት D. በአህዳዊ አስተዳደር

59. ከመንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ የህግ የበላይነትን በማስከበር ረገድ ቀዳሚ ተደርጎ የሚጠቀሰው ተቋም የቱ ነው?

A. የእምባ ጠባቂ ተቋም B. የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን C. ፍርድቤት D. መገናኛ ብዙሀን

60. ከሚከተሉት ውስጥ የዴሞክራሲ ስርዓት መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው?

A. የእኩልነት መብቶች መከበር B. ለህግ የበላይነት መገዛት

C. የሰብአዊ መብቶች ጥሰት D. የመምረጥና የመመረጥ መብት መከበር